
# ለድብቅ TB መድሃኒት፡- Rifampin (RIF)

TB FREE KING COUNTY

ለ4 ወራት መድሃኒትዎን በቀን አንድ ጊዜ ይወስዳሉ።

ዕለታዊ ክኒኖችዎን በተመሳሳይ ጊዜ አንድ ላይ ይወስዳሉ።

ንቁ ላልሆነ TB መድሃኒት እየወሰዱ እንደሆነ ለሌሎች ዶክተሮችዎ ይንገሩ።



የTB ኢንፌክሽን አይነት፣ ድብቅ TB አለዎት። የTB በሽታ የለዎትም እና TBን ወደ ሌሎች ሰዎች ማሰራጨት አይችሉም። ይህ መድሃኒት ንቁ የTB በሽታን ለመከላከል ይረዳል።

| **መድኃኒት** | **የእንክብሎች ቁጥር** |
|---|---|
| Rifampin | |

**መድሃኒቶቼን ለ4 ወራት በየቀኑ እወስዳለሁ**



ጥያቄዎች ወይም የጎንዮሽ ጉዳቶች ካሉዋችሁ ነርስዎ ጋር ይደውሉ፡-

______________

Public Health Seattle & King County

# አቁም

TB FREE
KING COUNTY

መድሃኒትዎን ወዲያውኑ መውሰድ ያቁሙ እና ከዚህ በታች ያሉት ማናቸውም ችግሮች ካጋጠሙዎት የTB ነርስዎ ጋር ይደውሉ፦

- ትንሽ ወይም ምንም የምግብ ፍላጎት የለም
- የሆድ ህመም ወይም የሆድ ቁርጠት
- ማቅለሽለሽ ወይም ትውከት
- የኮላ-ቀለም ሽንት ወይም ቀጭን ሰገራ
- የቆዳ ወይም የአይኖች ቢጫ መሆን
- ቀላል ቁስሎች ወይም መድማት
- ሽፍታ ወይም ማሳከክ
- ከባድ አቅም ማነስ ወይም ድካም
- ትኩሳት
- የጭንቅላት ወይም የአካል ህመም
- መፍዘዝ
- በእጆችዎ ወይም በእግሮችዎ ላይ የመንቀጥቀጥ ወይም መደንዘዝ ስሜት

**ማስታወሻ፦ የእርስዎ ሽንት፣ ምራቅ ወይም እንባ ብርቱካናማ ቢሆኑ ምንም ችግር የለውም። ለስላሳ ኮንታክት ሌንሶች ሊበከሉ ይችላሉ.**

## ጠቃሚ ምክሮች ለRIF አወሳሰድ

- መድሃኒትዎን እንዲወስዱ ለማስታወስ ማንቂያ ያዘጋጁ
- በባዶ ሆድዎ መድሃኒትዎን ይውሰዱ
- አልኮል የሚጠጡ ከሆነ ሐኪምዎን ያነጋግሩ፣ አልኮል የጎንዮሽ ጉዳቶችን ሊያስከትል ይችላል
- ሌላ ስለሚወስዱት መድሃኒት ለሐኪምዎ ይንገሩ
- ጥያቄዎች ካሉዎት ነርስዎን ይጠይቁ